# የወጣት ተስፋዬ ተካልኝ የ23 ወራት የግፍ እስርና ግርፋት.

የጐንቻው!

ለወራት ሳይሆን ለዓመታት የተጠበቀችው ብርቅዬ ፀሃይ እንደ ባህር በተንጣለለው የአውሮፓ ሰማይ ላይ ደምቃ፤ሙቃ እየፈካች፤ የአገሬው አባወራና ቤተሰብ ሁሉ ልብስና 'ትጥቅ' አስፈትታ ከጠዋት እስከማታ በየቤቱ በረንዳና 'ጓሮ ግቢ' ይንገላወዳል። ወደ መንገድና ሱቅ የወጡት ደግሞ ለነገሩ ያህል ሥሥ ቀሚስ፤ከነቲራና ቁምጣ ተላብሰው ሰንበትን በደስታና በመዝናናት ይፍነሸነሻሉ።

እኔም እጥር ምጥን ያለ ለብሼ በጓሮ በኩል ካለው ግቢዬ የዛሬ አስር ዓመት የተከልኳት ባህር ዛፍ ስር ጠለል ብዬ እንደተቀመጥኩ አሳቤ እንደለመደው የአገሬን ሰማይ ፍለጋ በድኒን ጥሎኝ ነጐደ። ሰንበት ሲጣላ ከዓርብ እሮብ ይከፋል እንዲሉ እህል ውሃ አላሰኘኝም ይልቅስ የራበኝ፤የጠማኝ ዘወትር በጉጉት የምጠብቀው የእለቱ 'የኢሳት ዜና' እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት ጠብቄው በኢንተርኔት አልተለቀቀም፤ቅር እያለኝ እጄን ለእንቅልፍ ሰጠሁ።

እነሆ ዛሬ እሁድ ረፋድ ላይ ከአገሬ ጥሪት ባህር ዛፍ ስር ቁጭ ብዬ ልቦናዬ በሰመመን መንኩራኩር ሲክንፍ በከፊል እየሸኘሁ፤ቀኝ እጄ ወደ ኪሲ ረዘመና ሞባይል ስቦ የእሳት ድህረ ገጽ ላይ አፈጠጠ። የ'**ሰብአዊ መብቶች**' የሚለው ፕሮግራም እያንዳንዱን ፊደላት ጥይት በሚመስል ድምጽ እየበጣጠቀ ሲጀምር ስደተኛውን ቀልቤን ከሃሳብ ግልቢያ ቀየደው፤ትንሽ ቀደም ባሉት ጊዚያት በጨረፍታ የሰማሁት ዘግናኝ የእስርና የግርፍት ሰቆቃ የሚያስቃኝ ቃለ መጠይቅ ነበርና ከቤተሰብ የቀረበልኝን የሻይ፤የቡና፤የቁርስ ግብዣ ሁሉ አስትቶ ሁለመናዬን አሳስሮ አኖረኝ።

የወጣት ተስፋዬን እጅግ ዘግናኝ በደል፤አሳዛኝ ግፍ ሳዳምጥ መግለጽ በሚያስቸግር ሁኔታ ሃዘን ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛነትም ጭምር ይሰማኝ ጀመር፤ ሳላውቀው እንባ ካአይኖቼ ይወርድ ኖሮ ይኸንን በቅርብ እርቀት ያስተዋለች ሴት ልጄ ቀርባ ስታጽናናኝ አቅመ ቢስ ወይም ሆደ ባሻ ሆኘ አልነበርምና የማነባው ከጉልቤቴ ቁጭ ስትል በተናወጠ ሃሳብ ውስጥ ያለው ህሊናዬ አልሰከነ ኖር ሳላስበው በቁጣ ገፈተርኳት፤ ለካስ ልቤን ካደማው ሃዘን በበለጠ ሁለንተናዬ በንዴት በቁጭት በእልህም አሮ ተክኖ ቋፍ ላይ ኖሬያለሁ። እንዲህ አድርጌው በማላቀው አድራጐቴ የደነገጠችውን ልጄን መልሼ አቅፌ በማባበል ከየት ጀምሬ የቱን ስንቱን ላስረዳት፤ደግሞስ ይኸንን የመሰለ ጭካኔ ሰው ይፈጽማል ያውም 'ደግ፤ደጉን' ስለምተርትላት ልዩ አገር ኢትዮጵያና ጨዋ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ። በዚያ ቅጽበት የተገረፈ እራቁት ገላ የሚያሳየውን ከሞባይ ስዕል አይታ ኖር 'ምክንያቱ' ግብቷታል። ዘወትር የአገሬን ዜና ስሰማ ትንሽ ራቅ ብዬ እንደምሰማ ታውቃለችና ስለ አጠቃልይ የአገራችን ጉዳይ ለነገሩ ቤተሰቤ ባይታወር አይደሉምና።

ቀጥላም፤ 'አባዬ የአገራችን ሰዎች እንዲህ ሲሰቃዩ ስታይ የሚሰማህን እገምታልሁ ሁሉንም ባላውቅ አገራችንና ወገኖቻችን ከዚህ የተሻለ ይገባቸዋል ስትለኝ አሁን በእርግጥ 'ሆድ ባሰኝ'፤ የሆድ ብሶቴ ምክንያት ይህችን የመሰለች አገር ነው የምናስረክባችሁ የሚለው ስሜትና በደለኛነት፤ተጠያቂነት የበለጠ እየከነከነኝ ነበር።

ብዙ ጉዳዎችን ለእለቱ የወጠንኩ ቢሆንም አሁን ቀልቤን የሰረቀው ትልቅ ጉዳይ የሰማሁት የወንድሜ የተስፋዬ ተካልኝ የእስር ሰቆቃ፤ከዚያም በላይ አሁን ያለበትን ስስማ፤ስገምት፤የበደሉት ቀነኞች የሚቀማጠሉባትን ኢትዮጵያ ሳነጻጽር ጭራሽ እረፍት አጣሁ፤

በውስጥ ልቦናዬ ጆሮ የሚስመነመነው ድምጽ፤ ሲቃን እያቀረበ፤እያራቀ የሚያሳየኝ የህሊናዬ ዓይን አፍጦ ሁለመናዬን ረብሾታል። ከሃሳቤ ጋር እየተሽቀዳደምኩ ወደ ጥናት ክፍሌ አመራሁ፤ እነሆ መጫጫርም ጀመርኩ በአይኔ አልፎ አልፎ የሚመነጨውን የእልህ እንባ እየጠራረግሁ።

> *"… አሁን ሽንቴን መቆልጣጠር አልችልም፤ ውጪንም ውስጤን ለ23 ወራት በግፍ ገርፈውኛል፤ አሸባሪ፤ግንቦት ሰባት፤ተቃዋሚ፤ምናምን ነህ እያሉ፤ያልሆንኩትን የማላውቀውን ሁሉ እየዘረዘሩ፤እየቀባጠሩ፤ጀርባዬን፤እግሬን፤እካሌን በሙሉ በኤሌክትሬክ ሾክ እያቃጠሉ ጠብሰውኛል፤የጀርባዬን አጥንት ደብድበው አድቅቀውታል፤ብልቴንም ቀጥቅጠው አኮላሽተውኛል፤ኩላሊቴን ደብድበው የህሊናና የአእምሮ ቁስል ጋር በቁሜ ገድለውኛል፤*
>
> *የዘመኑ ኀጭ ለባሾች፤ በአንድ ጎደሎ ጠዋት ሳይነጋ መጥተው በሬን ደብድበው ከእንቅልፌ አዋክበውና አፍነው ከወሰዱኝ እለት ጀምሮ በየእስር ቤቱ እያንከራተቱ በጨለማ፤እስኪ ደክማቸው፤ ሱሳቸው እስኪወጣለቸው ደበደቡኝ።*
>
> *እነሆ በድንጋጤ እንደ ነገሩ የለባስኳትን አንድ ልብስ ለሁለት ዓመት ብቻ ለብሼ በላዩ ላይ እስኪታልቅ አቅምለውና አሳክከው ሰብአዊ ክብሬን እጅግ፤እጅግ አዋርደው፤ ተነግሮ የማያልቅ በደል ፈጽመውብኛል የዘመኑ የቤተመንግሥት ሽፍቶች፤ወያኔዎች፤*
>
> *ታዲያ እንዲህ አዋርደው የሚያረጉኝ ቢጠፉቸው ከነቀመለች እራፊ ጨርቄ ጋር ዝዋይ አልባሌ ቦታ ጣሉኝ፤ አንዲት ነገር ትንፍሽ ብትል አንተን ብቻ ሳይሆን ዘመዶችህን ሁሉ ከምድረ ገጽ ድምጥማጣቸውን እናጠፋለን" ብለው፤የዚህ ዓለም 'ጌቶች*

በአንድ ወቅት የተከበረ የቪኦኤ ጋዜጠኛ ቃለ መጠይቅ ያደረገላቸውን እንዴት ደፍረህ ጠየቅኸን ብለው ሲያስፈራሩ የተደመጡት የፓሊስ አዛዡ ‘እንኳንስ አሜሪካን አገር መንግስተ ሰማያትም ቢሆን አምጥቼ እዚህ በእስር እቀፈድድሃለሁ’ ብለው የደነፉት ደንቆሮ ትዕቢተኛ አዛዦች መንጋ በህሊናዬ ሲተራመስ ሁለመናዬን እየኮሰኮሰኝ፤እየጎራበጠኝ ።

*‘አሁን መዋያ፤ማደሪያ የለኝም፤ ምንታደርገዋለህ! በእርግጥ ከእንግዲህ ሞት አልፈራም! ግን እንደ ሰው እንደ ወንድ፤እንደ ኢትዮጵያዊ በቁሜ ክብሬን እሻለሁና ለህክምና ብቻ የወገኖቸን እርዳታ እማጠናለሁ።’*

ቀጥሎም በእርሱና በወላጆቹ ላይ ቀድም ብሎ የደረሰባቸውን በደል ሲያስረዳ፤ ይኸ የወራሪ፤የወንበዴ ፤የወያኔ ቡድን በዘራው የዘርና የጐሳ ቁርሾ ወላጅ አባቱን በአርባባ ጉጉ ቢያጣም እናቱ ወደ ናዝሬት ተሰደው ጠላ እየሸጡ አስተምረው ለአካለ መጠን እንዳደረሱት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ተመርቀ በሙያው አገሩን ወገኑን እንደ አንድ ኩሩ ኢትዮጵያይዊ በብቃትና በቅንነት ሲያገለግል እንደነበረ ትልቅ ህልምና ተስፋም እንደነበረው ጨምሮ ገልጿል።

*‘እኔ በሕይዎቴ አንዷት ብርጭቆ ሰብሬ አላውቅም እንኳን አገር ላፈርስ፤መንግስት ልገለብጥ ሽብርተኛ፤ነህ፤ብለው እመን፤እያሉ እየተፈራረቁ ለ23 ወራት ገረፉኝ። እኔ ግን ያላደርግሁትን አድርጌያለሁ ብዬ አላምንምና ከፈለጋችሁ ግደሉኝ አልኳቸው፤ አፍነው ከወሰዱኝ እለት ጀምሮ ዘመድ፤ወገን፤ባልደረቦቸ በተለይ ምስኪን ወላጅ እናቴም ሳታውቅ በየመግረፊያ ዋሻቸው እያንከራተቱ ቀን ከሌሊት ገረፉኝ፡ በቁሙ ሙቷል ብለው ሲያምኑ መንገድ ዳር ጥለውኝ ሄዱ።’*

የዚህ የወንድማችን፤የወጣት ተስፍዬ ተካልኝ ገድልና የመንፈስ ጽናት እጅግ፤እጅግ የሚደነቅ፤የሚከበር ተምሳሌ ነው፤ ከጥንት ጀግና አባቶቻችን ቅድመ-አያቶቻችን የተወረሰ ቅባ ቅዱስ በግርፍት፤በግፍ፤በእስራት፤በእንግልት በጥላቻ የማይሰበር የማይንበርከክ የጥንካሬ ሚስጥር:: ተስፋዬ የጀርባ አጥንቱን ቢሰባብሩት፤ደሙን ቢያዋዡት፤ገላውን በኤሌክትሪክ ቢጠብሱት፤ስጋውን ቢተለትሉት፤መንፈሱን ግን አልሰበሩትም፤ጽናቱን አልተቋቋሙትም አንዱ ወጣት ጀግና ደርዘን ገራፊ፤አስግራፊዎችን ረታቸው 23 ለ 0።

ተስፋዬ እንደ ማንኛችንም ትዳር ይዞ፤ቤተሰብ መስርቶ፤መውለድ መክበድ ልጅ ማሳደግ ተፈትጥሯዊ ሕግጋትና ፍላጎቱም ነው፤ ነገር ግን ለመግለጽ በሚዘገንንና በሚከብድ አኳኋን ባደረሱበት የብልት ጥቃት ለጊዜውም ቢሆን ይኸ እንደማያስጨንቀው ይናገራል፤ ነገር ግን ተስፋዬ አንድና ሁለት ልጆች ብቻ ሳይሆን እንደ ወንድ፤እንደ ሰው እንደ አባት በአራአያነቱ መቶ ሺህ ልጆችን ያፈራል፤ለአምላክ የሚሳነው ታዕምር የለምና አገሩ/አገራችን ነጻ ስትወጣ፤ ውልዶ፤ከብዶ፤ ይኖራል፤ ለሁሉም ይበቃል። ምንም እንኳ እንደ እርሱ አባባል በተለይ ቅድሚያ የሚሰጠው አንገብጋቢ ጉዳይ ቢኖርም።

*‘አሁን ቅድምያ እምሰጠው በአዲስ መንፈስ ለነጻነት መታግልን ነው፤ሌላ ወገኔ እንደ እኔ የጸረ ሽብርተኛ አዋጅና ሰበብ ሰላባ እንዲሆኑ አልፈልግምና፤ደግሞስ በአሁኗ ኢትዮጵያ ልጅ መውለድ ለባርነት ካልሆነ ምን ዋጋ አለው።’* ይላል፤

*በወንድማችን ላይ የደረሰውን የግፍ እስራትና ግርፋት ዘግናኝ ሰቆቃ እየቀፈፈውም ቢሆን በከፊል እያስታወሰ ቋንቋ ሊገልጸው የሚችለውን ያህል ነግሮናል፡ ለምንሰማ ጆሮ ላለን ኢትዮጵውያን ሁሉ:: ሁሉንም ለመገመትና ለመረዳት እጅግ ይከብዳል፡ ከሁሉም በላይ ይኸንን የመሰለ ሰቆቃ ለመፈጸም የሚያስችል አረመኔያዊ ጭካኔ 23 ዓመት ነግሰው አቅማቸውን፤ትዕቢታቸውን፤ሁሉ በአደባባይ አሳይተው ዘርፈው ከብረው አልፎላቸው ጥላቻቸው እስካሁን የማይለዝብላቸው ምን ያህል የታወሩ፤የዘቀጠ፤ የረከሰ ትንሽነት፤ የአውሬ ስብዕና ቢኖራቸው ነው።*

*አወ! አይካድም፤ ወያኔዎች በርካታ ለሆዳቸው ካደሩ ቀላዋጮች ጋር ተቧድነው፤ተደራጅተው በአገራችን መዲናና በየሃገሪቱ ከተሞች ሁሉ የብዙ ሚሊሆን ዶላር ፎቅ ገንብተዋል፤በውጭ አገራት ባላቸው የባንክ ሂሳባቸው ከአፍ እስከ ገደፉ በዶላር ሞልቷል ‘እኔ ከምትኩ ሰርዶ አይብቀል በሚል ብሂል 3ቢሊዮን ዶላ ሰርቆ አሸሽቶ እንደመከነው ጣዖታቸው፤ ሚሊሆን ኢትዮጵያዊ በርሃብና በችግር እየተጠራሞተ የመለመኛ ንግድ ፈቃዳቸው አድርድገውታል፤በሙት ጥኝ ምስል(ጉፍል) ወተት እንደሚያልቡበት አይነት መሆኑ ነው።*

*ትናንት በረባሶ ተጫምተው የተጣጣፈ ቁምጣና ቅራቅንቦ አንግበው የመጡ ‘የትግራይ ነጻ አውጭዎችና’ እና ግብረ አበሮቻቸው እነሆ ዛሬ በጣም ውድ የሆነ የቅንጦት መኪናና ሊመዝን እያሽከረከሩ ይንቀባረራሉ፤ በአገራችን እራሳቸውን ቁጥር አንድ ዜጋ አድርገው ከቤተ መንግሥት፤ቤተመቅደስ፤ እስከ መጨረሻው የንግድ ተርታ ‘ግልት’ ድረስ በበላይነት አጠቃለው። በሆደ ሰፊነት፤በወገናዊነት ታግሶ በሰላማዊ መንገድ ለሚማጸናቸው ሕዝብ ያላቸው ንቀትና ክብረ ቢስነት እጅግ ከመጠን አልፏል።*

*በተመሳሳይ ሁኔታ ከሞት ተርፎ ‘ ትዕንግርቱን’ ካካፈለን የቀድሞውና የጀግናው የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባልደረባ ከካፒቴን ተሾመ ተንኮሉ ወዲህ ተስፋዬ ተካልኝ አንድ እንደ ቅርጣን የተረፈ ሩህያ/ነፍስ ነው። በቁማቸው እነደተቀበሩ፤እንድታሰሩ፤ የሞቱን ሺህ ወገኖቻችን አምላክ ቀን ሲወጣ ይቆጥራቸዋል፤አሳሪ፤ግራፊዎቻችንምን በዚሁ በቃችሁ እንበላቸው።*

*ተስፍዬ አሁን ያለበት ሁኔት እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሳስብ ነው፤በአምላኩ እየተማጸነ ከአንድነት ዘቦች፤ጋር ተጠግቶ ለጊዜው እንደሚያድር ስሰማ በአደጋ አፋፍ ላይ እንዳለ ይሰማኛል፤ የፎከሩበት ገዳዮች ሌላ ጠንካራ ዜጋ ከሚያድኑበት ውሎ ሲመለሉ ከደከመ አካሉ ጋር የምትመናተል ህይዎቱን በአፍታ ቢቀጥፏት በኢትዮጵያ የ’አፓርታይድ ገዥዎች’ ማንም ከልካይ እንደሌላቸው ይሰማኛልና ሰጋሁ፡፡ በዘጠና ሚሊዮን ወገኖቹ መካከል መሸሸጊያ አጥቶ ሲንከራተት ማዬት ሌላ ቁጭት አዘዘብኝ፤በበዳዮቹ ብቻ ሳይሆን በጅምላ በሚጋዘው መንጋ ሁሉ።*

*ለተስፍዬ ጥሪ እንድንደርስ ተማጽኖውን እጋራለሁ የግሌንም በአፋጣኝ አደርጋለሁ። ለተስፋዬ ለአራዓያነቱ፤ለጽናቱ፤ለጥሪው እንዲሁም በሚሊሆን ለሚቆጠሩ 'ተስፍዬዎች' የማይደርስ እራሱን ለባርነት የሸጠ፤ያሻሻጠ ደንገጡር ነውና ቢኖርም ባይኖርም እርባና የለውም።*

*እነሆ በዘመናችን ለውጥ ፈጠንጠን ያለ ነውና፤ግብጻዊያን በቅርቡ ለሁለተኛ ጊዜ በብዙ ሚሊዮን አደባባይ ወጥተው ሌላ ንጉስ ገረሰሱ  ትክክለኛ ዲሞክራሲ በመሻት፤ምንም እንኳ የእነርሱን እጣ ፈንታና የዘለቄታ ነጻነት ለራሳቸው ብንተወውም ጽናታቸው፤ሕብረታቸው፤ቅንጅታቸው፤ቁርጠኝነታቸው በእጅጉ ያስቀናል።*

*ወደ ግብጽ አገር በገፍ እንደ አባይ ወንዝ የሚፈሰው የለውጥ ማዕበል አገራችንን ምድረ በዳ ሊያደርጋትምና ባያጎርፍም፤እያካፋና እያቆረ ለመሆኑ ሰማያዊ ደማምኖ ሸገር አደባባይ ቦይ ቀዳጅ ሆኗል፤ እነሆ አንድነትም የሶስት ወር ያላሰለሰ የበልግና የክርምት ደቦ ጠርቷል፤በውጭም፤በውስጥም የሚያጉተመትምው ኃይል ከመተራመስ ወደ አንድ አቅጣጫ መፍሰስ ጀምሯል፤በፍቅር በጽናት በአንድነት። እነሆ እንደ ባቢሎናዊያን በእርግማን መደናቆራችንም ረገብ ብሎ መደማመጥ ጀመረናል፤መጠላለፍም አቁመን መደጋገፍ ጀምረናል፤ እጅ ለእጅ ተያይዘን መደረሻችንን ሰንቀን ማዝገም ጀምረናል። ጥሩ ተስፋ ሰጭ ጅምር ነው።*

*ገዥዎቻችንም በትንሹ ሙዳይ የቋጠሩት የነገር ሚስጥር አፈትልኮ እየወጣ በማዕዳቸው ዙሪያ በመጎራረስ ፈንታ መነካከስ በመመራረቅ ፈንታ መረጋገርም እየሰማን በእብሪት የተጠጣ አቢሾ አናት ላይ ወጥቶ እያሳከራቸው ነው። አንጃውና አንጃኞች ተበራክተዋል፤ተደርጓቾችም የአራጆች ስለት ተሞርዶባቸዋል እነሆ አብዮት ልጇን ትበላለችና ሆዳቸውን እያከኩ ነው። መሰሪዎች በፋኖነታቸው ያበጠሩትን ጎፈሬ ተሚጢና ሸግቶ ባዶ እራስ ቅላቸውን ያሳሻቸዋል፤ የ23 ዓመት ወንጀላቸውም ንስሃ የማይሸረው ሆነና በእንቅል ፈንታ ቅዥት ነው አዳራቸው።*

*ወያኔዎች ሰባት ሆነው አፍላ የጠነሰሱት የተንኮል ሴራ በርሃ ወርደው፤ዋሻ መሽገው ሺህዎችን አስከደው፤አሳስተውና አወናብደውም የጊዜ ሎተሪ ሲወጣላቸው በአሳቻ ቀን አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ዘው ብለው በመግባት እራሳቸውን አደላድለው አገር ቆርሰዋል፤ ታርክ ከደዋል፤ ሕዝብ አዋርደዋል፤እምነት አርክሰውዋል፤ ይኸ የግፍ ዘመን ሊያከተመ ነው። በቃ!በቃ!*

*እነሆ እኛ ዘጠና ሚሊሆን ሆነን ከየደጃፋችን ትንሽ ዝንዘር ተራምደን አደባባይ እንውጣና ነፃነታችንን እንቀዳጅ!*

*አሁን ቀኑ፤ዘመኑ፤ጊዜው የኢትዮጵያዊያን ነው የትግል፤የድል፤የነፃነትና የእርቀ ሰላምም ነው።*

*በርቱ! እንበርታ! ኢትዮጵያን ተረካቢ ትውልዷ፤በእስራት፤በግፍ፤በድብደባ ተኮላሽቶ  አገራችን ባዶ/ወና እንዳትሆን አሁን ለወገኖቻችን በአንድነት እንድረስላቸው!*

*ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ለዘላለም ይኖራሉ፤በክብር፤በጸጋ፤በሰላም፤በነጻነትና በፍቅር!*

http://www.zehabesha.com/atrocious-torture-and-inhuman-treatment-in-ethiopia-part-1-to-4-video/

*የጐንቻው!*		yegonchaw@yahoo.co.uk		*07/07/2013*